# ጅብ እና ኣህያ



ኢትዮጵያ እዚህ ላለችበት ደረጃ እንድትደርስ ኣህያ የተጫወተችው ሚና ሁሉ እትዮጵያዊ የሚዘነጋው ኣይመስለኝም። ኣገልግሎቷ ቢታሰብ በእድገቱ የመጀመርያ ተጠቃሚ መሆን የነበረባት ኣህያ ነች። ዳሩ ግን የኢትዮጵያ ነገር ሁሌ ያልሰራልሽ በላ ነዉና በረከቱ ልጭላዳ፡ ለኣንበሳ፡ ለነብር፡ ለጅብ ወዘተ ሲተርፍ ኣህያ ግን ቄራ ነው የተቀበላት። ድሮ ማር ነበር የማይጥማት። ኣሁን ደግሞ ሂወት ሆነ።ህዝቡ ባቀረበው ኣቤቱታ ቄራው እንደሚዘጋ ይነገር እንጂ ባለ ሃብቱ የገዛቸዉን 300 ኣህዮች -ልብ በሉ? ኣርዶ እንዳልጨረሰና ወደ ዉጭ ለመላክ ሃ ብሎ ስራውን እንደጀመረ ነው በቅርቡ የተዘገበው። ምክንያት መሆኑ ነው፡ እርዱ መቼ እንደሚቆም እግዜር ይወቀው። እስከዛው ግን በቁጥር ላይ ቁጥር እየተጨመረ በቀጣይነት መታረዷ ኣይቀሬ ስለሆነ ኤሎሄ ድረሱልኝ እያለች ነው፡፣ ሰሚ ከተገኘ።

ሃይማኖትን፡ በባህልን፡ በተመለከተ በኣገሪቱ ላይ የሚያሳድረው ኣሉታዊ ትጸኖ ወደጎን እንተውዉና ኣህያን በማረድ ኢትዮጵያ የምታገኘው ትርፍ ምንድን ነውሕ ካለስ የኣገር የገንዘብ ምጣኔ -በጀት? ቀዳዳ ወይም የዉጭ ምንዛሪ እጥረት ምን ያህል ነዉ የሚሸፍነውሕ የግለሰብ ኪስ ሞልቶ ሊሆን ይችላል። በመንግስት ደረጃ ሲሰላ ግን ኋሰላሳ ዲናርቃ ነው። ሰላሳዉ ዲናር ደግምፕ ትቶልን የሄድው ነገር ቢኖር ጦስ ነው። ትቶልን የሚሄደዉም ከዚህ ኣይለይም። ጉዳዩ የእምነትና ነው። ፡ኣህያ ማር ላይጥማት ይችላል። ሞት ኣይሰማትም ማለት ግን ኣይቻልም፡ ከድሮ ጀምሮ ነው የምታቀው። ምስክር ካስፈለገ ጅብን መጠየቅ ነው። እናም ብትማር ፡ከሞት ብትታደግ ደስታው ያህያ ብቻ ሳይሆን ለፍትህ ለቆመና ለሃገሪቷም ጭምር ነው። ቅዱስነቱ የሚመጣው ኣድርግ ያልተባለዉን ከማድረግ በመቆጠብ ነው። የኦርቶዶክሱ፡ የእስላሙ፡ የካቶሊኩ፡ የጰንጤው መስሃፍም፡ የሚያስረግጠዉ ይህ ነው። የቀሳር ለቄሳር .እንደተባለው።

ለምዶበት ነው ኣይኔ ጥላሽ የሚከተለዉ

ወይስ ኣእምሮየ ኣንችን የሚያሰላዉ

በይና ተበይ በማይለይበት

ሂወትና ጤዛ ኣንድ በሆነበት

ኣዚህ ፊቴ ቁሞ ተገትሮ የማየው

ኣንቺ ነሽ ኣህያ ወይስ መንትያሽ ነው

ኣህያ

ብዥታም ኣይደለም ኣይንህ የፈጠረው

ቅዠትም ኣይደለም ኣእምሮህ የሳለዉ

መንትያም ኣይደለም ሰይጣን የገተረው

እኔ ነኝ ኣህያ የምታቀኝ ድሮ

በስደት ጎዳና ቢብስብኝ ኑሮ።

ጅብ

ሜዳና ተራራዉ ጎራ ሸንተረሩ

ሁሌ ኣረንጓዴ ሳርና ቅጠሉ

ምንጩ ኩሬው ሃይቁ ወንዝና ጅረቱ

በየመኣዝኑ የሚግኝበቱ

ይህን ኣገር ትቶ  የሚያስመርጥ  ለስደት

እኛ የማናዉቀው ምን ተገኘ ድንገት

የጤና ኣይመስለኝም ካልሆነ የእብደት።

ኣህያ

ኣገር የሚያስብል በሃገር የሚኮራ

ሲኖር ነው በሰላም በህብረት ሲሰራ

ሲያሳልፉት ሃዘኑም ደስታዉም ተካፍሎ በጋራ

ኣንዱ ያሻዉ ሲያረግ ፈላጭ ቆራጭ ሆኖ

ለላዉ በስቆቃ ሲኖር መብቱ ታፍኖ

ከተኖረ ባገር ምኑ ሃገር ሆነ

ቀን ተሌት እንደ ሬት ኑሮ እየመረረ።

ጅብ

ዬብላኝ እንጂ  ሰው ነኝ ለሚለው ሰው

በረባ ባልረባ ጠብ እየፈጠረ ወንድ ከወንድም ጋር ለሚጨራረሰው

በሌለ ልዩነት ልዩነት እያመጣ

በንሮው በእድገቱ ለምያመጣዉ ጣጣ

ኣኝቺ ምኝ ጎደለሽ ኑሮ ምን በደለሽ

ባገር ሳር ኣልጠፋ ረሃብ ኣልወረረሽ

ስልጣን ኣትፈልጊ የርስት ሙጉት የለሽ

ኣገር ምጥቃ በእድገት ኣልፎልሻል ብለን በተደሰትንበት

ሃገር ኣስጠልቶ የሚያስመኝ ስደት

የጤና ኣይመስለኝም ካልሆነ የእብደት።

ኣሀያ

ቢነጠፍ ኣስፋልቱ ሃር የመሰለ

ቢገድቡት ግድብ ዉቅያኖስ ያከለ

ቢበዛ መኪናዉ እንደኣሸን ቢፈላ

ቢገነቡት ፎቁ ቢያክል ተራራ

ካልተረፈ ትንሽ ለኔ ለድሃይቱ

ምኑ ነው ዉለታው የቱ ነው እድገቱ።

እከፋለሁ እንጂ ለምን ኣልከፋ

ወገኔ ሲክደኝ፡ ሲዳርገኝ ለሞት  የጣልኩበት ተስፋ  ፡

ጅብ

ኣስመሰልሸው እሳ ባንቺ የተጀመረ

በዚህ ኣለም ኑሮ ያልሞተ ማን ኣለሕ

ከመቃብር በላይ ዘላለም ይኖረ

ኣይቻልም እንጂ ቢሆን ጥሩ ነበር

ትሰድዶ መኖር ሞት በሌለበት ሃገር።

ኣሀያ

ኣይቅሬ እንኳ ቢሆን መሞት በያሉበት

በግዜር እጅ ያምራል እራሱ ባለበት

ከምታልፍ ሂወት ብሰው እጅ ተገድላ

 በሰው ኣገር ሄዶ ለሳምንትም ቢሆን  ይሻላል መሰንበት ፈልጎ ከለላ።

ጅብ

ወደኔ ክሆነ የሚያምመላክተው ጣቱ

የችግር መነሻ የስደት ምክንያቱ

ኣልተው ጅብነቴን የሰጠኝ ጽጋ ነው ሲያድል ለፍጥረቱ

ደግሞስ ኣንድ ሁልት ዉርንጫ ቢገበር ምናለ

እሾህ እየወጋው ጮቃ እያዳለጥው ሰዉ ይሞት የለሕ

ኣህያ

ምነው በሆነልኝ እንዳፍህ እንደለመድኩት ድሮ

እመሹበት ማደር ላንድ ጌታ ኣድሮ

በሰላም መተኛት ኣንድ ሁለት ገብሮ።

ድሮ የነበረኝ  ሁለት ጠላት ነዉ

ወይ ሰባራ ኣጥር ትል የቦረቦረዉ

ወይ ሰነፍ እረኛ እግዜር የበደለዉ

ኣሁን ግን ወዳጄ ሁሉ ተቅይሮ

ጠላቴ ሰው ሁኖኣል ሰዉነት ቀይሮ።

ጇብ

ላትቅይረዉ ነገር እግዜር ለወሰነዉ

ከሰው ጋር ተጣልቶ እሰው ኣገር መሄዱ ከምን ሊያድንሽ ነዉሕ

መልክ ይቀይር እንጂ እዚያም ያለው ሰው ነው።

ስቃይ በዛ ብለሽ ችግር በዛ ብለሽ

ኣምጸሽ እንደሆን ኣልገዛ ብለሽ

እዛዉ መታገል ነው የፍትህ ያለህ ማለት ከህዝቡ ጋር ሆነሽ።

ኣህያ

እግዜር ሲፈጥረኝ ከጥዋት ከጥንቱ

ሰው ላግለግል ነው የተፈጠርኩቱ

ድካሙ ኣይደለም ያስቆጣዉ ስሜቴን

ረሃቡ ኣይደለም የነካዉ ኣንጀቴን

ጉዳዩ ወዲህ ነው የሚያስደነግጠው

የሚያስብል እግዚኦ ህሊና ለሰጠው

ለዚህ እንዳላበቃሁ ኣዝየ ኣንጠልጥየ

ሰጠኝ ኣሳልፎ ጠላቱ ለሆነው።

ጅብ

ምንድን ነው የምትይዉሕ እረ በይ መላ

ምን ይገኝ ብለሽ ነው ክሃሰት ዉንጀላ

በረት እየሰራ ኣጥር እያጠረ

በጠላት ፈርጆ እኛን ባባረረ፡ እኛን በገደለ

ብቆመ ጥብቅና ኣንቺን ባከበረ

ሰው ይስቅብሻል ስትይ ሰው ገደለ

ቢሆን ኣይደለም ወይ ያንቺ ኣጋር ሆኖ

ፎቁ እየተመኘነው

ኣስፋልቱ እያማረን

ዳርጎን የቀርውለበረሃ ኑሮ ።

ኣህያ

ቀበሮ ኣለች ሲሉ ሰው ማመን ቀብሮ ንው

ልቤ ይበግን ነበር ሰው ሰደበች ብዬ

ስም ኣጠፋች ብዬ ኣንተ እንደምትለዉ

ኣሁን ግን እዉነታው ሳየው መለስ ብዬ

የሷ ምሬት ሳይሆን የኔ ብግነት ነበር ሚዛን የጎደለዉ ፡ ስሜት የወጠረው።

የታጋይ ደሳለኝ የዛ የሰማእቱ

የኒያ በባድሜ ፈንጅ የረገጥቱ

ባድዋ በኦጋዴን ታምር የሰሩቱ

ኣያት ቅም ኣያቴ ያደረጉት ገድል

ያሳለፉት ስቃይ የተወጡት ችግር

እይተዘከረ እየተወደሰ እኖራለሁኝ ስል

ስጠብቅ እፎይታ የደስታ ህልም ሳልም

ራሴው ግዳይ ሆንኩኝ የነ ጉድ ኣያልቅም።

እንኳንስ መወድስ እንኳንስ ሽልማት ሞትም  ተከልክየ እግዘር የፈጠረው

ተሰራልኝ ቄራ ለኔም እንደ በሬው

እንዲህ ኣይነት ክህደት ስም ማጥፋት ነው ካልከዉ

ፍትህ ኣያጣህም ፈርዱን ላንት ልተው።

ጅብ

መንገድም ሲጓዙት ቀና የሚሆነው

ጥላቻ የሌለው፡ ስሜት የማይገዛዉ ቀና ልብ ሲኖር ነው

ህቅነት ከሌለዉ ሚዛን ከጎደለዉ ቢጓዙት በርቀት

ከመሆን ኣያልፍም እንቅፋት የሞላው ችግር የበዛበት።

ትምህርት ቤት ኣይደለም ሚገበይበት እዉቀት

ፋብሪካም ኣይደለም እቃ ሚሰራበት

ግኝትም ኣይደለም የሚያሳይ ፈጠራ

ኣገር  የማያውቅው ራእይ የሚያጋራ

ምን ሆንኩኝ ቢሎ ነው ምንስ ቢያገኝብት

በተቀደሰው ኣገር ያህያ ማረጃ ቄራ የሰራበትሕ

ኣህያ

ባውቀው ጥሩ ነበር ባጤነው  ምክንያቱ

ባእድ ለማስደሰት እኔን ማስከፋቱ

ርቦታል እንዳልል ያለፈው ይብሳል

ችግርም እንዳልል ካለፈው ቅንሷል

በግ ፍየል ባልጠፋ ኣህያ የሚያርድበት

ቢሆን ይሆናል እንጂ በጁ መጥተዉበት።

ጅብ

ጥላቻ ኣያዋጣም እግዘር በፈጠረሻ

ኣንቺዉ በጣም ከፋሽ ለማስከፋት ብለሽ

ረሃቡ ጥማቱ ሁሉም ያልበገረዉ

እምነት ኣጎደለ  እያልሽኝ እኮ ነውሕ

ኣህያ

እምነት ድሮ ቀረ መሞት ለመኑበት

ሂወትን ማሳለፍ ኣንዴ ከማሉበት

ጥዋት የማሉትን ማታ ከተሻረ

 ቢምሉት ሺ ጊዜ ምኑ እምነት ሆነ

ባቋሙ ካልጸና እምነቱ በሚለዉ

ኣዉሬዉና ሰዉ  ምን ልዩነት ኣለውሕ

የሰው መሰረቱ ነዉና እምነቱ

ታሪክ የሚቆምበት ባህሉ ሃይማኖቱ

እምነት ትሸቀንጥሮ  ለሆድ ከታደረ

ሰዉነት ከጠፋ እምነት ከጎደለ

የዛ ሰዉ የምትለው ስዉነት የት ኣለሕ

እምነት ከጠፋ ቆየ ሰው ሰዉነቱ ካጣ

በሽታ በዝቶበት በስኳር ያመጣ ።

ጅብ

ኣየ ያንቺ ነገር መላ ቅጡ ጠፋ

ሰው ጠፋ ትያለሽ ሰዉነት ባልጠፋ

ጠቢቡ ፈላስማው

መሃንዲስ ከያኒው

ደራሲው ጠበቃው

ሐሐባንቺ እንዴት ይደርሳል እንዲህ ኣይነት በደልሕ

እንደምን ትያለሽ እምነት ኣጎደለ ኣንቺን ሊያስከፋሕ

ኣህያ

ይማር እንጂ ዲግሪዉን ይጫነው

ይወቅ እንጂ ጥበቡን ይካነው

ያክም እንጂ ቀዶ ይጥግነው

ትምህርት ልብ ኣይሆን ሰው ልብ ከሌለው።

ኣወቀ የምትለው በጣም የተማረ

በፈረንጂው  ቋንቋ ፊደል የቆጠረ

ይመራል ተብሎ ስልጣን የተሰጠው

ወንበር ተቅምጦ ወንበር ነው የሚግጠዉ።

ሲታገል የመጣዉ ፍትህ ለማስፈን ብሎ

በዱር በበረሃ ስንት መስዋእት ከፍሎ

ስልጣን በያዘ ማግስት ወንበር ላይ ከወጣ

ጊዜም ኣልወሰደ ወድያዉኑ ታመመ  በስኳር የመጣ ።

እንኳንስ ለያግዝ  ለኣህያ ኣፍዋ ለተዘጋ

ሊረዳ ላጋሩ ኣብሮት ለተዋጋ

ለራሱም ኣልሆነ ስኳር ትጠናዉቶት ይሰቃያል ባልጋ ።

**የተማረ ይግደለኝ ድሮ እንዳልተባለ**

**እንዳላሳየ ራእይ ማየት ያስቸገረ**

**ኣይኖቹ ታውረዉ  ተለክፈው በስኳር ጊዜ በፈጠረው .**

**ኣጠገቡ ያለም ማየት  ተቸግሮ ማንነህ እያለ ነው።**

ጅብ

ሙሁርስ እሺ ይሁን እንበል ግድ የለው

ሳይኖረው ኣንድ ኣቋም  ኣንድ እምነት ሳይኖረው

የሰጡትን በልቶ ተኝቶ የሚያድር ነው።

ቄሶቹ ሸሆቹ እንያ በሃይማኖት ጸንተው

ገስጸዉ ገዝተዉ የሚሉት ኣንተ ተው

ወዴት ቢሄዱ ነው ምንስ ቢነካቸው

ለህልፈት የበቃሽ ኣንቺ ኣገልጋያቸው።

ኣህያ

የትኛው ቄስ ነው ኣንተ ቄስ የምትለው

የትኛዉን ሸህ ነው ኣንተ ሸህ የትለው

እንያ ጸልየው እግዜር የሚሰማቸው

እንያ ሸምግለዉ ህዝብ የሚቀበላቸው

እነሱ እኮ የሉም ብዙ ጊዜ ሆናቸው

ኣቤት ኣቤት ብለን ኣብዮቱ ገድሎኣቸው።

ኣዲሱ ትውልድ እንደሆነ ተቅባዩ ኣደራ

ብሉይ የሚጠላ ነው በቅርስ የማይኮራ።

እንኳንስ ጸልዮ ሊያሰጥ ምህረቷ

ኣገልጋይ ናት ብሎ ሊለምን ለጌታ

ምናብና እዉነት ፡ እየተጋጨበት

ሳይንስና ሃይማኖት፡ እየተምታቱበት

መሪ ይፈልጋል መሃሪ ጠፍቶበት ።

ኣይበለዉ እንጂ መኣቱን ኣያምጣ

ያለ ኣይመስለኝም ከልብ ጽልዮ ከእሳት የሚያወጣ።

ጅብ

ጸላይ ከጠፋ ምጽኣት ካዳመነ፡ ሃጢእት ከነገሰ ከበዛ ኲነኔ

ኣትጸልይም ራስሽ ኣትለምኝም ለግዜር ብለሽ ምሃረነሕ

ኣህያ

ምነው ኣያጅቢ ያውቃል የሆድ ሲባል ይሰማል ጽሎቱ

የስዉን ነው እንጂ ኣይደል የኔ ኣይነቱ

ይወደኛል በርግጥ ስጥቶኛልም ክብር ለማንም ያልሰጠው

ዳሩ ምን ያደርጋል

ኣልከለክለው ነገር ሰው በሰራዉ ሃጢኣት ፡ እኔም መዘፈቅ ነው.

ተዛዛት ኣይፈጽም በምነቱ ኣይጸና

ምህረቱ ሳይጭርስ ዳግም ይዘቅጥና ይጠራል መከራ።

ኣትሽምግለኝ እባክህ ቅሪ ኣትበለርኝ ተወኝ ልሂድበት

እኔም ቁርጤን ልወቅ ኣንተም እረፍበት

ሺ ጊዜ ቢከፋ  ስደት ከዚህ ኣይብስበት ።

ትበላኝም እንደሆን ደስታዉን ኣልችለው

ነውር በጠፋብት ዘመን

ክህደት በበዛበት

ባደግሁብት ሃገር ፡ በለመድኩት ቀየ በወጉ መበላት በግዜር መባረክ ነው ።

ጅብ

እረ በስመ ኣብ በይ እግዜር በፈጠረሽ

በቀውጠው ሰኣት ሰው በከዳሽ ዘመን እንዲህ በቸገረሽ

ከቶም ኣታስቢ ይበላኛል ብለሽ ።

ለዚች ላጭር ጊዜ ነገ ለምታልፈው

ለበስባሹ ስጋ ኣፈር ለሚለብሰው

ስጋ ኣገኘሁ ብዬ ስጋሽን ብዉጠው

የኔንም በተራው ትል ነው የሚጠብቀው ።

ስጋሽ ስጋዬ ላይሆን ነፍስሽ ነፍስ ላይሆነኝ

ኣንቺኑ ብገድል ሟቹ እኔው ራሴ ነኝ

በድርጊቱ እያዘንኩ ሰው በሚሰራዉ ስራ

እኔ ብገባበት ከመሆን ኣያልፍም የከሃዲ ስራ ።

ደግሞስ ቢጥይቀኝ ለእግዜር ምን ልበለው

ትውልድስ ምን ይበል

ታሪክ ምን ይበለኝ

ማተቤን ስበጥስ ማተብ እንደሌለው ።

ይልቁንስ ሂጂና ኣረፍ በይ ድካሙ ይዉጣልሽ

ስደቱ ሁሌ ኣለ ነገም ትሄጃለሽ

ወይ ታድሪ ይሆናል ሃሳብሽ ቅይረሽ

ክብር በሃገር ፡ ሞት በሃገር ብለሽ ።

ወይ የፈጠረሽ ገታ በሁኔታሽ ኣዝኖ

የገዳይሽ ምኞት ኣቅጣጫ ቀይሮ

የበዳይሽ ተእቢት በጸጸት ቀይሮ

ያስጥልሽ ይሆናል ከመኣተ ሞቱ

በልደቱ ኣንድትይ፡ በምስቅሉ እንድትይ ዕሆሳእና እንድትይ ኣንቺም በምህረቱ።

# ጎዲፍ ተፈሪ

የሰዉን ሂወት ለማቃናት በዱር በገደሉ  ደከመን ሳይሉ እያገለገሉ ሂወታቸዉን ላጡት  ታዳጊ ኣጥተዉ በየቄራዉ ለታረዱትና በመታረድ ላይ ላሉት ላኣገሬ ኣህዮች  መታሰብያ እንዲሆን የተጻፈ፡፤ መስከረም 29ዕ2010 ዓሐም።  *ተገፀጸረገፀሰ12ፄየቷሀጸጸ.ቾጸመ* -ይቀጥላል?